# የኪነቱ ንጉሥ

ልሳነ ጣዕመ ቃናውን ከዲያቆን ቅላፄ ወስዶ፣
አሰባበሩን ከወፍ ዜማ እንጉርጉሮውን ከዱር እረኛ አስገድዶ ፤
"ዋይ ዋይ" ብሎ እንደ አስለቃሽ ተለማምዶ፤
እንደምትፈትል ሴት ወይዘሮ ዓይነ ልቃቂት ጥሎ፣
እንደሚገላምጥ ጎረምሳ ወደላይ ወደታቸ አንከባሎ፣
እንደ ሰራቂ የሰፈር ዳንዴ ያየውን በጥቅሻ አስኮብልሎ፣
የከረመ የወሊሶ አንበሳ፣
በዘፈኑ እጅ እንዳላስነሳ፡
ቀኑ ደርሶ ዘፈን አቆመ መረዋ ድምፁ ሳሳ፣
ደከመው አሉኝ ገላው ዛለ እግሩም ሳይቀር እጅ ነሳ።

ጥላሁን ያገር አድባር የኪነት መደላድል፣
የማትችለውን አትጀምር የሌለህበትን አትከጅል፣
ያልሰራብህን ዝምታ አታምጣ ጸጥ ብለህ ሰው አትበድል።

ኸረ አሉ እንደ ጳውሎስ ዘፈንህን ቀርቶ ለቅሶህን፡
ለመስማትየሚፈልጉ ለማየት የሚጌጉ ዓይንህን፣
አሉህ የግል ምርኮኞች ዘመን የሚቆጥሩብህ፡
እንደ ሰገሌ እንደ አድዋ እድሜ የሚያሰሉብህ።
ዜማህን ከጌደኛ ከፍቅረኛ ከቤተ ዘመድ፣
የሚያገናኙ ዓመታቱን ከቅላጼህ ድምጸ ሞገድ፣
ተነሳ እንጂ እንዴት በድንገት ከመድረኩ ተገፍተህ ትወርድ።

ጥላሁን የፍቅር ምርኮኛ፥ ጥላሁን የኪነት ምኩራብ፣
በዝምታህ ስንቱ ተንካ በኩርፊያህ ምእመን ሊራብ?
የምትወድህ ምን አለችህ የናፈቃትን ምን አልካት?
እንደ ተናደደ ደብተራ ድምጽህን በዝምታ የቀጣሃት፣
ተስፋ እንደቆረጠ ወታደር ቀኑን ያጨለምክባት፣
እንደ ተማረከ መኮንን ዝምታን የተካህባት፣
ኢትዮጵያን እንዳላሞገስክ "ሃገሬ ሃገሬ" እንዳላልካት፣
መርገጥ ተሳነህ መሰለኝ ከርሰ መህጸኗን መርጥካት።

ያገሩን ሴቶች በመላ "ሞናሊዛ" እንዳላልካቸው፣
ውበትን እንዳልፈለፈለክ ፍቅርንም እንዳልፈለጥከው፣
ምሬትን እንዳላወጣህ ቀረርቶን እንዳልሸለልከው፣
"ድምጻዊ ዘፋኝ ነኝ" ብለህ ሞትን እንዳልቃኘሽው፣
ዛሬ ምን ተፈጠረ ድምጽህን በድንገት ገደልከው፣
በአስፈሪ መቃብር ለስነህ፡ ኪነትን አብረህ ቀበርከው።

ጥላሁን  እባክህ አትጨክን ድምጽህ እንደሆን ምትክ የላት፡
“እንክርዳድ” ብሎ  ለማቀንቀን  “መለያየት ሞት ነው” እሚልባት፡
የፍቅርን ቦታ አጠያይቆ  መውደድን የሚያሳምራት፡
ግድ የለህም በኔ ይሁንብህ ካንተ ሌላ ኪነት ሰው የላት፣
እያመመው የሚስቅ ካልጋ ሆኖ  የሚያዜምላት፣
ኪነት ካላነንተ  ማንም የላት፡
ይልቅስ አርካፉኔ በላት፣
አንተው አሳድገሃት መልሰህ አንተው አትግደላት።
ቅርስ ነውና የውድ ሃገር ከፍ አድርገን እናስቀምጣት፡
እንደ ጠዋት ፀሎት እንድገማት፣
እባክህ ቃልህን አትለጉማት፣
ቅላጼህን አትቅበራት፣
የኪነት ዓይንህን አታጨልም እንዳኮራችን እንኩራባት፣
ጥላሁን ቃልህን አትግደላት.........................


ተኮላ መኮንን
ዳላስ ቴክሳስ

04/ 21/ 2009